# የመተማመን መትነን
# (Trust Evaporation)

ገለታው ዘለቀ
April 6, 2016

በመጀመሪያ ደረጃ መተማመን (Trsut) ስንል የአንድ ህብረተሰብ የጋራ ሃብት ወይም የማህበራዊ ካፒታል ዋና ኣካል መሆኑን እናንሳ። በአጠቃላይ ማህበራዊ ካፒታል ስንል ደግሞ ልክ እንደሌሎቹ የሰው ልጆች ካፒታል የሚታይ ነው። ለምሳሌ የገንዘብ ካፒታል፣ የሰው ካፒታል (Human capital) እንደምንለው ማህበራዊ ካፒታልም ካፒታል ይባላል። ካፒታል ነው እንደንል የሚያስችለን ምክንያት ኣንድም ልክ እንደሌሎቹ ካፒታሎች የሚመረት (Produce የሚደረግ) መሆኑና ለተለያዩ የማህበረሰብ ልማቶች ኢንቨስት የምናደርገው ሃብት በመሆኑ ነው። እነዚህ ተፈጥሮዎቹ ከሌሎች ካፒታሎቻችን ጋር ያመሳስሉታል።

የሰው ልጅ የሚያመርተውና ለተለያየ ልማቱ የሚጠቀምበት ይህ ማህበራዊ ካፒታል ልክ ሌሎች ሃብቶችን ለማምረት አቅደን እንደምንሰራው ተጠንቅቀን ልናሳድገውና ልንይዘው በኣስፈላጊው ቦታና ጊዜ ሁሉ በኢንቨስትመንት ላይ ልናውለው የሚገባ ትልቅ ሃብት ነው።

ኣዳም ስሚዝ የተባለው እውቁ የምጣኔ ሃብት ተጠባቢ በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ አንድ የማይታይ እጅ (Invisible hand) አለ እንደሚለው የማህበራዊ ሃብት ዋና ኣካል የሆነው መተማመን በሰው ልጆች እድገት ውስጥ ኣንዱ የማይታይ እጅ መሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ነው። በጠቅላላው ማህበራዊ ካፒታል ህብረተሰብ የሚያመርተውና ለህይወቱ የሚጠቀምበትም ነው ብለናል። ታዲያ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ማህበረሰቡ ራሱ የሚፈጥራቸው ሶስት ዓይነት ማህበራዊ ካፒታሎች እንዳሉ የማህበራዊ ካፒታል አጥኒዎች ይነገራሉ። አንደኛው አዎንታዊ ማህበራዊ ካፒታል ሲሆን ሁለተኛው አሉታዊ ማህበራዊ ካፒታል ይባላል።

ሶስተኛ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ገለልተኛ ማህበራዊ ካፒታል (Neutral Social Capital) ሊሆን ይችላል። አዎንታዊ ማህበራዊ ካፒታል (Positive social capital) የሚባሉት ከህብረተሰቡ ባህል፣ ወግ ልማድ፣ ሃይማኖት አካባቢ የሚመነጩ ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ እድገት ኣስተዋጾ ያላቸው ሃብቶች ናቸው። ለምሳሌ ስራን የሚያበረታቱ ስነቃሎች፣ እርስ በርስ መተማመን፣ የፍቅር ሃብት፣ ታማኝነት፣ ምክንያታዊ የሆነ የቁጠባ ባህል፣ የመረዳዳት ባህል ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው።

በአንጻሩ ኣሉታዊ (negative social capital) የሚባሉት ደግሞ አንድ ህብረተሰብ በግልጽም ይሁን በህቡዕ እየተለማመዳቸው ያሉ ነገር ግን ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ እድገት ኣደናቃፊ የሆኑ ናቸው። ለምሳሌ ያህል ብናነሳ አንዳንድ ኣደገኛ ባህሎችን መጥቀስ እንችላለን። ስራን የማያበረታቱ ስነ ቃሎች፣ ሃሜት፣ የጫት ባህል፣ ሌሎች በባህሎቻችን ውስጥ ያሉ እንደ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ግግ ማውጣት፣ እንጠል መቁረጥ፣ ሰውነትን በስለት መተልተል፣ ከባህል ጋር ተያይዞ በሴት ልጆች ላይ የሚፈጸሙ በደሎች፣ በህጻናት ላይ የሚፈጸሙ ባህላዊ ግድፈቶች ወዘተ. ህብረተሰብ የፈጠራቸው ነገር ግን ለህብረተሰብ እድገትና ምርታማነት ኢንቨስት ሊደረጉ የማይችሉ እንዷውም ጎታችና ኣደናቃፊ ናቸውና ኣሉታዊ ማህበራዊ ካፒታል ሊባሉ ይችላሉ። አፍሪካ ውስጥ ተቆጥሮ የማያልቅ ኣሉታዊ ካፒታል ያለ ሲሆን ይህንን ለመቀነስ ትልቅ ዘመቻ ያስፈልጋል።

ኣለበለዚያ የሰባዊ እድገትን ከፍ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ቶሎ ግቡን ኣይመታም። ሌላው ካፒታል ገለልተኛ የሚባለው ሲሆን ይሄ በሰው ልጆች ሁሉንተናዊ እድገት ላይ የጎላ ኣሉታዊ ተጽእኖ የሌለው ሊሆን ይችላል። እንዲህ ኣይነቶቹን ለጊዜው ችላ ብሎ ኣሉታዊ ካፒታሎችን የመቀነስ ኣዎንታዊ ካፒታሎችን የማሳደግ ስራ ያስፈልጋል።

ለመግቢያ ስለ ማህበራዊ ካፒታል ይችን ያክል ዳራ ከሰጠን ከማህበራዊ ካፒታል ውስጥ ኣንዱ ዋና ነገር መተማመን ነው። በዚህ ዙሪያ ጥቂት ውይይት እናድርግ። መነሻችንም ይሄው ነውና። ማህበራዊ ካፒታል ስንል፣ መተማመንን፣ የህብረተሰብ ኔትወርክን (Networks)፣ ለጋራ ጥቅም በጋራ ለመስራት መስማማት፣ መደጋገፍ(Reciprocity) ፣ ልማዶች (norms) የሚመለከት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ መተማመንን (Trust) ብቻ መዝዘን የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ ብንገመግም ጥሩ መስሎኛል።

በኢትዮጵያ ሁኔታ የመተማመን ሃብታችንን በሶስት ኣገራዊ የመተማመን የፍሰሰት ኣቅጣጫዎች መገምገም እንችላለን። እነዘህ ሶስት የመተማመን መፍሰሻዎች

1. የግለሰብ መተማመን (Interpersonal trust)
2. ቀጥታ መተማመን (Vertical trust)
3. የጎኖሽ የቡድን መተማመን(Cross cultural interpersonal trust)

ናቸው።

በነዚህ ዙሪያ የኣገራችንን የመተማመን ሃብት ወቅታዊ ይዞታ ለመገምገም ኣንዳንድ ጥናቶችን ለኣብነት ማየት መልካም ነው። የግለሰብ መተማመን ደረጃን በኢትዮጵያ ሁኔታ ስናይ በዚህ ሃብት ኢትዮጵያ ብዙ የቀደመቻቸው ኣገሮች ኣሉ። ለምሳሌ ያህል ታዋቂው የምጣኔ ሃብት ተጠባቢ ማክስ ሮዘር ባጠናው ጥናት መሰረት የኢትዮጵያ የዜጎች መተማመን (interpersonal trust) ከብዙ ኣገሮች ሲነጻጸር መሃል ላይ ነው። በዚህ የመተማመን ሃብት ውድድር ኢትዮጵያ ከቀደመቻቸው ኣገሮች መካከል ፈረንሳይ፣ቡልጋሪያ፣ማሌዢያ፣ኢራን፣ሞሮኮ፣ሰርቢያ፣ማሊ፣ጆርጂያ፣ስፔንና ቱርክም ይገኙበታል።በዚህ ጥናት መሰረት ኖርወይ፣

ስዊድን፣ ፊንላንድ ከአንድ እስከ ሶስት ደረጃን የያዙና የመተማመን ሃብታቸው ሙላት ያልጎደለባቸው ሲሆን አጠቃላይ ናሙና ተወስዶባቸው ከተጠኑት ሃምሳ ስድስት ኣገራት መካከል ኢትዮጵያ ሃያ ስድስተኛ ደረጃ ላይ ናት። መተማመን ከህብረተሰቡ መሃል የተነነባቸው የተባሉትና መጨረሻ ላይ የተቀመጡት ኣገራት ቱርክ፣ሩዋንዳና ትርኒዳድ እና ቶቤጎ የተሰኙት የደቡብ ኣሜሪካ ደሴት ናቸው። ኢትዮጵያ በኣንጻራዊነት መሃል ላይ የሚገኝ ውጤት ያላት ሆኖ እናያለን። በርግጥ በግል የምንታዘበውም ይህንን ነው የሚመስለው። ይህንን ካየን በሁዋላ የቀጥታ መታመን (vertical trust) ደረጃችንስ የት ነው? የሚለውን ለመገምገም ዝንባሌ ሊያድርብን እንደሚችል እሙን ነው።ቀጥታ መታመን ስንል ህዝብ በመንግስት ተቋማት ላይ ያለውን እምነት የምንለካበት የመታመን ኣቅጣጫ ነው።

ቀጥታ የሆነው የመተማመን ወይም የመደገፍ ካፒታላችን የሚገለጽባቸው አንዳንድ ኣንጻራዊ ጥናቶችን ማየት ጥሩ ነው። ከነዚህ ጥናቶች ውስጥ የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናልን ኣመታዊ ጥናቶች ማየት ለግንዛቤ ይረዳናል። እንደ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል (Transparency International ) ጥናት ኢትዮጵያውያን በፖለቲካ ስልጣን ኣካባቢና በህዝብ ተቋማት ኣካባቢ ያላቸውን ዝንባሌ ስናይ መታመን ተንኖ እናያለን። ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ባጠናው መሰረት ቀደም ብለን ያየናቸውና ኢትዮጵያ በእርስ በርስ መተማመን (Interpersonal trust) የቀደመቻቸው ኣገራት ሁሉ በዚህ በቀጥታ መተማመን ደግሞ እንደገና በከፍተኛ ደረጃ ቀድመዋት ይታያል። ኢትዮጵያ ውስጥ 33 በመቶ የሚሆን ህዝብ ብቻ በመንግስት ተቋማት ላይ እምነቱን ሲገልጽ ስልሳ ሰባት በመቶ የሚሆነው ህዝቧ በመንግስት ተቋማት ላይ ኣይታመንም ወይም ኣይደገፍባቸውም።

በኣጠቃላይ ስናይ እንደ ሃገር መታመን በመንግስትና በህዝብ መካከል የለም ወይም ተንኖ ሄዷል ማለት ነው። ከፍ ሲል እንደጠቀስነው ለምሳሌ ፈረንሳይን ብናይ፣ ስፔንን ብናይ ተቋሞቻቸውን በከፍተኛ ሁኔታ ይደገፋሉ። ፈረንሳይ ውስጥ ሰባ በመቶ የሚሆነው ህዝብ ተቋሙን መንግስቱን ያምናል። በአንጻሩ ኢትዮጵያ ደግሞ የተገላቢጦሽ ነው የሚታየው። ሌሎች ጥናቶችን ብናገላብጥ ለምሳሌ ያህል የዓለም የብልጽግና ደረጃ መለኪያ (Legatum prosperity Index) የሚያወጣውን ጥናት ብናይ ኢትዮጵያዉያን በፍትህ ላይ በጣም ዝቅተኛ መታመን (Very low confidence) ነው ያላቸው ይላል። በአንድ ሃገር ውስጥ በተለይም ዋና ዋና በተባሉት ተቋማት ላይ ማለትም፣ በፍርድ ቤት፣ በሲቪል ሰርቪስ፣ በፖሊስ፣ በወታደሩ፣ሚዲያው ላይ እምነቱ ከተነነ ያ ሀገር በኢኮኖሚም ሆነ በሰባዊ ልማት ወደፊት መራመድ ኣይችልም። ይህንን ዝቅተኛ ማህበራዊ ካፒታል ይዞ በጥንድ እያደግን ነው ማለት ኣይቻልም።

የመታመን መትነን በመንግስትና በህዝብ መካከል ሲከሰት ተቃውሞዎች ይበዛሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ በዚህ መንግስት ጊዜ በስፋት የሚታየው ተቃውሞም  በመንግስት ላይ ከፍተኛ እምነትን ከማጣት የመጣ ነው። ባለፈው ጊዜ እንደተወያየነው አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ አሁን ስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ያለማልኛል ብሎ ሳይሆን በተቃራኒው ኣጥፊ ነው ብሎ ካመነ ያ ስርዓት ባስቸኳይ መለወጥ ኣለበት። የተነነን መታመን በቀላሉ ማዝነብ ኣይቻልም። የግድ ለውጦች መምጣት ይጠበቅባቸዋል።  አንዳንዴ ከህዝቡ መሃል ስለሚዲያ የሚነገር ነገር ኣለ።

ሚዲያውን ያለማመን፣ ለመንግስት ብቻ መሳሪያ መሆኑን ማመን፣ በመንግስትና በህዝብ መካከል መተማመንን ያተነነ ኣንዱ ጉዳይ ነው። የመንግስት በፍርድ ሂደት ውስጥ ጣልቃ መግባት በከፍተኛ ሁኔታ መተማመንን የሚያተን ተግባር ነው። በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞ በሚያሰሙ ዜጎች ላይ መትረየስና ከባድ መሳሪያ የታጠቀ ወታደር ማሰማራት በመንግስትና በህዝብ መካከል መታመንን እያተነነ ኣምባገነናዊ ከባቢን የሚፈጥር ነገር ነው። የሲቪል ሰርቪሱ ሴክተር እድገት የሚሰጠው፣ የሚቀጥረው በፖለቲካ ታማኝነት መሆኑን ህዝብ ሲደርስበት መተማመን ይተናል።

እንዲህ መተማመን የተነነበት ኣገር በአምስት ኣመት ትራንስፎርሜሽን እቅድ እናሻሽለዋለን ማለት ሌላ የቀረች ጥቂት እምነት ካለች እሷኑ ጨርሶ ለማትነን ነው። ቀጥታ መታመንን ከሚያሳዮ ሌሎች አንጻራዊ ጥናቶች ስናይ ለምሳሌ ፍሪደም ሃውስ የሚያወጣቸውን ጥናቶች በየጊዜው ስናይ ኢትዮጵያ ነጻ ያልሆነች ኣገር ናት። መንግስትና ህዝብ የሚደባበቁባት፣ የሚጠራጠሩባት ኣገር ናት። ይህ ኣይነት መንግስት በተለይ ብዙ ብሄሮች ያሉበትን ኣገር ሲመራ ኣደጋው ዘርፈ ብዙ ነው።

ግጭቶች እንደ ጭስ ቀዳዳ እየፈለጉ ሲወጡ ኣንዳንዴ በብሄር በኩል እየፈነዱ ብሄራዊ ማንነትን እየሸረሸረ ይመጣል። የዚህን የቀጥታ መታመን ሃብታችንን ስናጤን በህዝብና መንግስት መሃል እንዲህ መታመን ተንኖ እንዴት ነው የምንኖረው? የሚል ኣስገራሚ ነገር ይነሳል። በርግጥ ያው ኣንድ ኣምባገነን ስርዓት በሃይል ያስተዳድራል። ነገር ግን ከዓመታቶች በፊት ኣዲስ ኣበባ ውስጥ ብዙ ሰው ይለው የነበረው ነገር ትዝ ኣለኝ። እኛ መንግስት የለንም ይል ነበር ህዝቡ። የምንኖረው በቤተሰብ ህግና በባህላዊ ተቋማት ነው ይሉ ነበር። መንግስት ስወለድም ስሞትም ኣያውቀኝም፣ ግብር ለመሰብሰብ ብቻ ብቅ ይላል የሚሉ ወገኖች ብዙ ናቸው።እነዚህ ወገኖች የውነትም በባህላዊ ተቋሞቻቸውና በቤተሰብ ህጎች ነው ብዙውን ህይወታቸውን የሚገፉት እንጂ ከመንግስት ጋር ያላቸው መስተጋብር እጅግ ቀጭን ነው።የማህበራዊ ዋስተና ቁጥር እንኳን የለንም።

በርግጥም ለአንድ ሃገር የዜጎች የእርስ በርስ መታመን መኖር ሃገርን ለመጠበቅ ይጠቅማል። ትልቁ ሃብትም ይህ ነውና መጠበቅ ኣለብን። መንግስት ዘላቂ ኣይደለም። መንግስት ሲቀየር ያ የተነነው መታመናችን ይመለሳል፣ ይዘንባል። ነገር ግን በዜጎች መካከል መታመን ሲጠፋ እሱ የበለጠ ኣደገኛ ነው። በቀላሉ ኣናመርተውም እንደ ሌሎች የፋብሪካ ምርቶቻችን በቀላሉ የምናመርተው ካፒታል ኣይደለምና።መታመናችንን ለማደስ ብዙ ጊዜ ይፈጅብናልና።

ወደ ሶስተኛው የመታመን ኣቅጣጫ እናምራ። በእኛ ሃገር ሁኔታ የመታመን ካፒታላችን በብሄር ዘለል ደረጃም መጠናት ኣለበት። ኣንድ የብሄር ኣባል ከሌላው ጋር ሲገናኝ በምን ያህል የመተማመን ደረጃ ይኖራል የሚለውን ማጥናት በጣም ኣስፈላጊ ነው። ይህን እንድናደርግ የሚያስገድደን ኣገሪቱ ኣሁን ያለችበትን የብሄር ፌደራሊዝም ከግምት በማስገባት ነው። የብሄር ፖለቲካ በሰለጠነበት ኣገር ተዋረዳዊ የመታመንን ካፒታል ደረጃ ማጥናትና ደረጃውን እያዩ በተለያዩ ዘዴዎች ይህን ካፒታል ለማሳደግ መሞከር ለሃገር ኣንድነትና ለብሄራዊ ማንነት ለምንለው ጉዳይ ጉልህ ሚና ኣለው።

ኣንድ የትግራይ ተወላጅና ኣንድ የኦሮሞ ተወላጅ በአንድ ዮኒቨርሲቲ ውስጥ በኣንድ ዶርሚተሪ ውስጥ ሲኖሩ በምን ያህል የመተማመን ደረጃ ይኖራሉ? የሚለውን ማጥናት ጠቃሚ ነው። ይህን በተመለከተ በኣሃዝ የተጠና ጥናት ማግኘት ኣልቻልኩም።

ይሁን እንጂ በአንዳንዶች ዘንድ የሚታየው ጽንፈኝነትና ወገንተኝነት ይህንን ሃብታችንን እንዳያተንብንና ልብ ከልብ እንዳያራርቀን ዜጎች ሃላፊነት ወስደው ሊያስብቡት ይገባል። ባህላዊ ቡድኖች ወይም ብሄሮች በባህል ልዩነቶቻቸውና በቋንቋ ልዩነቶቻቸው መቼም ኣይጋጩም። እንደዚህ የተጋጩ ቡድኖች ኣይኖሩም። የአኙዋክ ብሄርና የኑየር ብሄር ኣባላት ወይም የጉጂና የቡርጂ ብሄረሰብ ኣባላት ያንተ ምግብ ኣይጣፍጥም የኔ ይጣፍጣል፣ ያንተ ኣለባበስ ኣያምርም የእኔ ያምራል፣ ያንተ ዳንስ ኣያምርም የእኔ ያምራል፣ ያንተ ቋንቋ ኣይገልጽም የእኔ ይገልጻል በሚል ጦርነት ኣይገቡም። የባህልና የቋንቋ ልዩነት በቡድኖች መካከል ያለን መታመን ኣያተነውም።

ብዙ ጊዜ ቡድኖች ግጭት ውስጥ የሚገቡት ይህ ባህላዊ ስብእናቸው የፖለቲካ ጥብቆ ሲለብስ ነው። ፖለቲካው የሚፈጥረው የቡድነኝነት ስሜት ልዩነትን እያራገበ ሲሄድ በኣስተዳደር ጉዳይ በተፈጥሮ ሃብት ጉዳይ ግጭት ውስጥ ይገባሉ። ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት ዘመናዊ ፖለቲካ የምታራምድ ሳይሆን ባህላዊ ፖለቲከኛ በመሆኗ ለቡድኖች ግጭት የተጋለጠች ከመሆኗም በላይ በቡድኖች መካከል የሚኖርን መታመን የሚያተን ከፍተኛ የፖለቲካ ሙቀት ስላለ ዜጎች ይህንን እንደተለመደው በሆነ ቴክኒክ መዋጋት ኣለባቸው።

እንደው ለአንባቢዎች ትንሽ ግንዛቤ ለመስጠት ያህል መታመን በተለያዩ ማህበራዊ ኣውዶች ውስጥ ሲታይ በሶስት ሊከፈል እንደሚችል ባለፈው ጊዜ ስለማህበራዊ ካፒታል ሳጠና ተረድቻለሁ። እነዚህ ሶስት የመተማመን ኣይነቶች የሚከተሉት ናቸው። ኣንደኛው የመታመን ኣይነት ህሊናዊ (Conscience Trust) ይባላል ። በዚህ ጎራ የሚመደቡ ሰዎች የእምነታቸው መሰረት ህሊና ነው። በቡድናቸው ውስጥ ልእልና እንዲያገኝ የሚፈልጉት ህሊናን ነው። የቡድኑ ኣባላት ለህሊና ከሰሩ ጤናማ የሆነ ግንኙነት ይኖራል ቡድኑም ትርፋማ ይሆናል ሩቅ ይሄዳል ብለው ያምናሉ። እነዚህ ወገኖች ህሊና ዋና የስጋት ኣሰውጋጅ (risk taker) ኣድርገው የሚያዩ ናቸው። በቡድናቸው መሃል ይሄን ያህል የጠነከረ ሲስተም ላይኖር ይችላል። ግን በፋይናንስ ጉዳይም ይሁን በሌሎች ጉዳዮች ህሊናን እያበረታቱ የቡድናቸውን ህይወት በጤና ሊመሩ ይሻሉ። ሁለተኛው ኣይነት ደግሞ ሃይማኖታዊ መታመን ይባላል። የዚህ ኣይነት የቡድን ኣባላት ደግሞ የመታመናቸው መሰረቱ የሚጣለው በቅዱሳት መጽሃፋቸው ትእዛዝ ላይ ነው።

ኣምላካቸው ዋና ስጋት ኣሰወጋጅ(risk taker) ተደርጎ የሚወሰድበትን ሁኔታ ያበረታታሉ። እነዚህ ወገኖች በኦዲት፣ በተጠያቂነት፣ በኣስተዳደራዊ ተሳትፎ ፈጣን ኣይደሉም። ይሁን እንጂ የተሻለ ጤናማ የመታመን ሃብት በጃቸው ይታያል። ሶስተኛው የመታመን ኣይነት ደግሞ ሲስተሚክ (Systemic trust) ይባላል። እንዲህ ኣይነት ሰዎች ስለ መታመን፣ ስለ ሞራል ጉዳይ ሲሰበክ ቢውሉና ቢያድሩ ኣይገባቸውም። ለነሱ መታመን የሚሰራው በጠንካራ ሲስተም ላይ ሲመሰረት ነው። ቡድኖች ሲሰባሰቡ የጠራ የስራ ክፍፍል፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ ኦዲት፣ ከፍ ያለ የኣባላት ተሳትፎ፣ ተጠያቂነት በጣም ይሻሉ። የእምነታቸው መሰረት የሚጣለው በነዚህ ጉዳዮች ጥራት ልክ ነው። እንተማመን እያሉ ቢሰብኳቸው ምንም ኣይዋጥላቸውም።

ዋና ሪስክ ወሳጅ (risk taker) የሚሰራ ሲስተም በመሆኑ መሃል ላይ የሚፈልጉት ነገር ይህንን ነው። ይህንን ክፍፍል ይዘን ወደ ከፍተኛው የሰው ልጆች ስብስብ ወይም ኣገር ስንመጣ ደግሞ ህዝብ በአያሌው ሲስተሚክ ሆኖ እናያለን።ይህ ማለት ህሊናዊ መታመንን ሙሉ በሙሉ ይጥላል ማለት ኣይደለም። ነገር ግን በጅጉ ህይወት ያለውን ሲስተም የሚደገፍ ሆኖ እናያለን። በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ በዘውዳዊ ኣገዛዞች ዘመን በንጉሱና በህዝቡ መካከል የሚኖረው የመታመን ድልድይ በኣብዛኛው ሃይማኖታዊ ነበር። ከኣምላክ የተሰጠ በመሆኑ ህዝቡ ስለተሰበሰበው ታክስ ኣይጠይቅም።ልምረጥ አይልም።

ዝም ብሎ ኣምኖ ይኖር ነበር። ዘመናዊነት ሲመጣ የሰው ልጅ በእውቀቱ ሲያድግ ደግሞ ወደ ሲስተም ትረስት ነው የመጣውና ያዘነበለው። በመንግስትና በህዝብ መካከል የሚኖረው ግንኙነት በግልጽነት፣ በኦዲት፣ በተጠያቂነት፣ በምርጫ፣ በፈቃድ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ህዝብ ይፈልጋል። ዴሞክራሲም ይህንን ወቅታዊ የሰው ልጆች ፍላጎት ለማሟላት የቆመ ካህን ነው። ዲክተተርስ የሚባሉት የዴሞክራሲን ልብስ ለብሰው ግን ደግሞ እንደ ንጉስ የሚኖሩት ዘመኑ የሲስተም ትረስት ዘመን ስለሆነ በዴሞክራሲ ስም ለመነገድ ነው። ይሁን እንጂ ህዝብ ደግሞ እውነተኛውን እምነቱን የሚጥለው የጸዳ ሲስተም ሲፈጠርና የተፈጠረው ሲስተም ግልጽነት፣ተጠያቂነትን፣ የህግ የበላይነትን ማንሸራሸር ሲችል ብቻ ነው።

በዚህ ዘመን መንግስታት ህዝቡን ዝም ብላችሁ እመኑኝ ማለት ኣይችሉም። የህዝብ ሉዓላዊነትን መቀበል ኣለባቸው። በመሃል የተሻለ ሲስተም ማምጣት ኣለባቸው። ህዝብ በመንግስት በኩል ሚስጥረኝነት መኖሩ ሲሸተው፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ሲጠፋ፣ የህግ የበላይነት ሲጠፋ፣ መንግስት ራሱ የማይጠየቅ ሲሆን ቀጥሎ የሚመጣው ነገር የመታመን መትነን አይደለም? መታመን ከህዝብና ከመንግስት መሃል ብድግ ብሎ ይተናል። ስለዚህ ነው መንግስታት ኣስር ጊዜ ስለግልጽነትና ተጠያቂነት ሲጥሩ የሚታዩት። የኢትዮጵያን ሁኔታ ስናይ ኣንዱ ለቀጥታ መታመን መትነን ምክንያት የሆነው ይሄው ነው። ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ የህግ የበላይነት ስለሌሉ እነሆ ዛሬ መታመን ተንኖ ኣልቆብናል።በአጠቃላይ በአሁኑ ሰዓት በሃገራችን ያለው በመንግስትና በህዝብ መካከል ያለው መታመን በቀላሉ ሊመለስ የማይችል በመሆኑ ኣገሪቱ ቶሎ ብላ ወደ ለውጥ መሄድ ኣለባት። ወደ ሽግግር መግባትና የህዝብን እምነት የያዘ ሌላ መንግስት ማቆም ያስፈልጋል።

መተማመን ሁለት ዓይነት ትርጉም ሊኖረው ሲችል ኣንዱ ከግብረገብ (Moral) ኣንጻር ያለው መተማመን ነው። በአብዛኛው በስብከት ልንገነባው የሚገባ የሞራል እሴት ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ያለው ግን ሳይንሳዊና በሚገባ ሊለካ የሚችል ነው። በዚህ ኣቅጣጫ መተማመን ሁለት ዋና ዋና ተለዋዋጮች(variables) ኣሉት። እነዚህም ዋስትና እና ስጋት ይባላሉ። በእንግሊዘኛው gurantees and risks ማለት ነው። መታመን የነዚህ የሁለት ተለዋዋጮች ስሪት ነው።

በአጭር ቃል መታመንን መገንባት ማለት ዋስታናን ማስፋትና ስጋትን መቀነስ ማለት ነው። መንግስት ዋስትናዎችን እያሰፋ ሲሄድ ስጋቶችን እየቀነሰ ሲሄድ ነው ህዝብ የሚደገፈው። በማንግስትና በህዝብ መካከል የሚኖረው የመተማመን ልክ የሚለካውም መንግስት ባሰፋው ዋትና ልክ ነው ማለት ነው። በዚህ ጊዜ ዜጎች መንግስታቸውን ይደገፋሉ። ይህ ካልሆነና ስጋቶች እየጨመሩ ሲሄዱ በመንግስታቸው ላይ ያለው መደገፍ ይቆምና ቶሎ ለውጥ ይፈልጉና ያምጻሉ። መንግስት በስልጣን ለመቆየት የሚለው ነገር እመኑኝ መልካም ኣስተዳደርን ተወያይተን እናመጣለን፣ ትንሽ ጊዜ ስጡን ነው። ይሄ ደግሞ ለህዝቡ ዋስትና አይሆንም። ሩብ ምእተ ዓመት ሙሉ ስልጣን ላይ ሆኖ በጥንድ ቁጥር ኣደግን እያለ ሲል የነበረ መንግስት አሁን በገጠሩ ከአስር ሚሊዮን በላይ በከተማውም እንደዚሁ ወደ ኣስር ሚሊዮን ህዝብ ለረሃብ ተጋልጧል።

ይህ ኣንዱ የመንግስትን እምነት ያተነነ ክስተት ነው። ትናንትና መቶ ፐርሰንት ኣሸነፍን ያለ መንግስት ስድስት ወር ሳይሞላው ብዙ ቁጥር ያለው የኦሮሞ ህዝብ ሜዳ ላይ ወጣ። በታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ተቃውሞ ነው። መንግስት ይህንን ሲያይ መሸነፍ ኣይወድምና የኔ የስራ ውጤት ነው ጠያቂ ማህበረሰብ ኣፈራሁ ይላል። በኣስራ ዘጠኝ ስልሳዎቹ የተነሳው ህዝባዊ ንቅናቄ ሃይለስላሴ ያፈሩት ጠያቂ ማህበረሰብ ነበር ማለት ነው? እሳቸው ይህን ሳያውቁ ነው ያለፉት። በደል የበዛበት ህዝብ ኣንድ ቀን በቁጣ ገንፍሎ መውጣቱ ተፈጥሯዊ ነው። የሆነ ነገር ሰርቶ ማሳየት ያልቻለ መንግስት ይህንን  የኔ የስራ ውጤት ነው ማለቱ ይገርማል። ህዝቡ ሰልፍ የወጣው እኔ በፈጠርኩት ዴሞክራሲ ነው ሊል ኣይችልም። እንዲያማ ቢሆን መንግስት ተቃውሞውን ባዳመጠ። በሰላማዊ ተቃዋሚዎች ላይ ጥይት ባላፈሰሰ።

ኣሁን ደግሞ የተያዘው ፈሊጥ የመልካም ኣስተዳደር ችግር ነው የሚል ነገር ነው፡፡ እውነት ነው የመልካም ኣስተዳደር ችግር ነው። የመልካም ኣስተዳደር እጦት ቀለል ያለ ችግር ነው ማለት ነው? መንግስት የሚባለው ነገር መልካም ኣስተዳደርን ካላመጣ ምን ይሰራል። መለወጥ ነው ያለበት። ስርዓቱ ራሱ በሙስና መረብ የቆመ በመሆኑ በምንም ኣይነት ሪፎርሜሽን ኣይለውጠውም። የኢትዮጵያ ህዝብም ከእንግዲህ በዚህ ገዢ መንግስት ላይ ያለችው እምነት ያለ ልክ ቀጥናለችና ለሃገር ኣሳቢ ወገኖች ሁሉ የሽግግር ጊዜ የሚፈጠርበትን ሁኔታ መምከር ይኖርባቸዋል።በህዝብና በመንግስት መካከል እምነት ከተነነ በሁዋላ የሚጠበቅ ነገር አይኖርም። ለውጥ የግድ ሊመጣ ይገባዋል።እግዚኣብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ።

ገለታው ዘለቀ
geletawzeleke@gmail.com